# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

**ልዩ እትም**

ቁጥር 1 ግንቦት 7 2000 ዓ.ም


# ግንቦት 7፤ የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ተመሰረተ። እልፎችን በማሰባሰብ ህዝብ የጀመረውን ትግል ከግቡ እንደሚያደርሰው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ገለጹ።

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ መስራችና አመራር አባል የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን በአጭር ጊዜ ለመመስረት የሚያስችል አዲስ የትግል ንቅናቄ መመስረቱን ይፋ አደረጉ።ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ለተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችም ጥሪ አቀረቡ።

ዶ/ር ብርሀኑ የንቅናቄው ልሳን ከሆነው "ግንቦት 7 ድምጽ" ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ "በምርጫ 97 የቀረቡትን የፍትህ፣ የዲሞክራሲና የነጻነት ጥያቄዎች ለመመለስ አዲስና ከወቅቱ ፖለቲካ ጋር የሚሄድ ሁሉን አቀፍ የትግል እንቅስቃሴ መመስረት ማስፈለጉን" ገልጸዋል። የአዲሱ ንቅናቄ ስያሜም ግንቦት ሰባት የፍትህ፣ የነጻነትና የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ እንደሚባል ተናግረዋል።

ግንቦት ሰባት የሚለው ስም ለምን እንደተመረጠ ዶ/ር ብርሀኑ ሲያስረዱ "ይህ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ብሎ ሙሉ ልቡን የሰጠበት፡በመረጥኩት መንግስት ነው የምተዳደረው ብሎ ፍላጎቱን ያሳየበት፣የመጀመሪያው የዲሞክራሲ ሂደት በመሆኑና ይህም ታሪካዊ ክስተት በኢህአዴግ መንግስት የተቀለበሰ ቢመስልም ያ የታሰበውና የተፈለገው ዲሞክራሲያው ስርአት መምጣቱ ፈጽሞ የማይቀር መሆኑን፡ህዝቡም በዚያን ጊዜ ያሳውን ፍላጎቱንና ስሜቱን እንዳይረሳው ለማስታወስ ተብሎ የተሰጠ ነው" ብለዋል።

ዶ/ር ብርሃኑ አያይዘውም አዲሱ ንቅናቄ ሰፊና አስፈላጊ የመታገያ መንገዶችን ሁሉ የሚጠቀም በመሆኑ ህዝቡ ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲያደርግና በተለይም ወጣቱ በግንቦት 97 ምርጫ ያሳየውን አስደናቂ ተሳትፎ በአዲሱ ንቅናቄ ስር ሆኖ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል። የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችም አንድ አገር መኖሩን እስካመኑና ዲሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት ፍላጎቱ እስካላቸው ድረስ የግንቦት 7 ንቅናቄ ኩሉም ጋር በቅንብርና በትብብር የማይሰራበት ምንም ምክንያት እንደማይኖረው ዶ/ር ብርሃኑ ገልጸዋል ። ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር የተደረገውን ቃለምልልስ በሚቀጥሉት ሳምንታዊ እትሞች በተከታታይ እናቀርባለን

## ጥሪ ከጋዜጣው አዘጋጆች

"የአወቀ ሕዝብ ነፃነቱን ይጠብቃል" ከሚለው ብልህ ግንዛቤ ተነስተን፣ ለነፃነት የሚደረገውን ትግል በሃቀኛ የመረጃ አቅርቦት ለማገዝ ይህን የሕዝብ ልሳን ይዘንላችሁ ቀርበናል። ጥረታችን እንዲሳካ የእናንተ ምክር፣ አስተዋጽኦ፣ ጥቆማ፣ መረጃ እና መጣጥፍ ወሳኝ መሆኑን ተገንዝባችሁ፣ ከአስፈላጊው ጥንቃቄ ጋር በተቀመጡት አድራሻዎች መልእክቶቻችሁን እንድታደርሱ ጋብዘናችኋል። በተጨማሪም ይህንን ሳምንታዊ ጋዜጣ በማባዛት ላልደረሰው ወገን በማዳረስ የዜግነት ግዴታችሁን ተወጡ። ይህን ማድረግ ራስን ነፃ ለማውጣት የሚከፈል አነስተኛ መስዋዕትነት ነውና። ነፃነት ብዙ ዋጋን የሚያስከፍል ቢሆንም ሁላችንም የድርሻችንን ከተወጣን ድሉ ቅርብ፣ ውጤቱም አርኪ እንደሚሆን እንደ እኛው በአምባገነናዊ ስርአት ውስጥ ወድቀው የነበሩ፣ ዛሬ ግን በነፃነት የሚኖሩ የበርካታ ሀገሮች ሕዝብ ታሪክ ያስተምረናል።

## የግንቦት 7 ንቅናቄ የፖለቲካ መርሃ ግብሩን ይፋ አደረገ፡


ዝርዝሩን በገጽ ሶሰት ይመልከቱ


## ሰለ ግንቦት 7 ድምፅ፤ ከአዘጋጁ

የግንቦት 7 ድምፅ ሳምንታዊ ልሳን፣ በግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የሕዝብ ግንኙነትና የቅስቀሳ ዘርፍ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን ነው። በዚህ ልሳን የእንቅስቃሴው አመለካከቶች፣ አቋሞችና እንዲሁም መሰል ጉዳዮች ይስተናገዱበታል።

ይህ ልዩ እትም የመጀመሪያው ነው። የእዚህ ልዩ እትም ትኩረት የንቅናቄያችንን መመሥረትና ይፋ መሆን ማብሰር ነው። በእዚህ እትም ለንቅናቂያችን የፖለቲካ መርሃ-ግብር አብዛኛውን ቦታ ሰጥተናል። በእዚህ መርሃ-ግብር ላይ ሁላችሁም ሰፊ ውይይት እንድታደርጉ ጥሪ አናደርጋለን። መርሃ-ግብሩ ያስቀመጣቸውን ቁምነገሮች በሚገባ ተረድታችሁ፣ ንቅናቄያችንን በተለያዩ ዘርፎች እንድታግዙ ጥሪ እናቀርባለን።

ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ የምናወጣው እትም በቋሚነት አራት ገጾች ይኖሩታል። ከመደበኛው የጋዜጣው ርዕሰ አንቀጽ ጀምሮ አጫጭር ዜናዎችንና ቃለ መጠይቆችን ይዘን እንቀርባለን። ህግና ሰብአዊ መብት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዩች የሚተነተኑባቸው ቋሚ አምዶች ይኖሩናል። በተጨማሪም የእናንተን የአንባቢዎቹን አስተያየት፣ የኪነጥበብ ውጤቶችንና ሌሎችንም አስፈላጊ ጉዳዮችን የምናስተናግድባቸው ተለዋጭ አምዶች ይዘን እንቀርባለን። ዓላማችን የግንቦት7 ድምፅን የወያኔን የመረጃ አፈና መስበሪያ ለማድረግ ነው። ስለራሳችንና ስለሃገራችን ጉዳዮች በነፃነት የመምከሪያ መድረክ ለማድረግ ነው። የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ የመሰባሰቢያና መደራጃ ሰፊ ድንኳን ለማድረግ ነው። ለመብት፣ ለነፃነት፣ ለብልጽግና፣ ለአንድነት፣ ለሀገር ደህንነትና ክብር ሰንል ለምናደርገው ትግል በጋራ አንድንነሳ አዋጅ መጎሰሚያ ለማድርግ ነው። ይህ ምኞታችን እንዲሳካ የናንተም ትብብር ማስለፈጉን አትርሱ።

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ
የቀድሞ የአዲስ ዜና እና
የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
Amesterdam
The Netherland

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ መሰፍን አማን፣ አቶ ቸኮል ጌታሁን፣ ሁሉም የቀንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ፡ ፡

# ርዕሰ አንቀጽ

## ነጻነት የቀደምቶቻችን ውርስ፣ ዴሞክራሲ የዜግነት መብት እንጂ የአምባገነኖች ችሮታ አይደለም

አዎን አዲስ ንቅናቄ መሥርተናል፣ ግንቦት 7 የሚሰኝ:: ካለፈው ልምድ ቀስመን፣ ከወደቅንበት ትቢያ ያነሳነውን ቁሻሻ አራግፈን:: ገዥዎቻችን በእብሪት ያጠሩልንን የመታገያ አጥር ሰብረን:: በሰውነታችንና በዜግነታችን ብቻ በሚገቡን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ላይ ቆመን:: ቀደምቶቻችን ለእኛ ነፃነት ሲሉ በከፈሉት የደም መስዋዕትነት የታሪክ ቅርሳችን ተማምነን:: መብት የፈጣሪ ጸጋ መሆኑን አውቀን:: ከእንስሳ የሚለየን ተአምራዊ ባህርያችን መሆኑን ተገንዝበን:: መብት የመለስ ትሩፋት፣ የሰብሃት ስጦታ፣ የበረከት ችሮታ አይደለም ብለን::

አዎን የታወቀው የመለስ ዜናዊ ሃገር የሚያሰክድ ዛር በሱዳን በኩል አዲስ የክህደት ግንባር ከፍቶ እየጨፈረ ባለበት አሳሳቢ ወቅት ነው ግንቦት 7ትን እንካችሁ ያልነው:: ህግ እኔ ነኝ፣ ልማት-ተኮር መንግሥት ነኝ፣ መብታችሁን በይደር አስቀምጣችሁ ልማታችሁን ተመልከቱ የሚል እብሪት የሃገሪቱን ማዕዘናት በወጠረበት ሰዓት ነው፣ ግንቦት 7ትን እንካችሁ ያልነው:: በ750 ብር ኩንታል ጤፍ፣ በ40 ብር ሊትር ዘይት፣ በ10 ብር ኪሎ ጨውና፣ የፋሲካ ዶሮ በቅርጫ የሚቀርብበት ጉደኛ ልማት ቀርቶ፣ በባሌስትራ ተቀይሮ በገዥዎቻችን የተዘረፈው የወርቅ ክምር ለእያንዳንዳችን ቢታደለን እንኳን ለመብታችን ልዋጭ አይመጥንም ነው የምንለው:: ከቀያችን ሰማይ አምላክ እርቆ፣ ሃገር ደርቆ፣ ጠኔ ሲያንደፋድፈን፣ እንሰንብት ብለን ጥንብ አንሳውን፣ አህያውን ሌላውንም እምነታችን የማይፈቅደውን ስንበላ አልተገኘንም:: በወተቷ ልጆቻችንን ያሳደገችን ላም ውለታ አክብረን አብረን ተራብን እንጂ አርደን ለመብላት አልደፈርንም:: የመንፈስ ጥንካሪያችን ሆዳችንን ሲገዛ እንጂ ሆዳችን የመንፈስ ጥንካሬያችንን ሲገዘግዝ አልታየም:: አለምንም ጉድ ያሰኘነው በእዚህ ጽናታችን ነው:: በዙሪያችን ሁሉም ተራ በተራ በባርነት ቀንበር ሲወድቅ፣ ተራ በተራ ለቅኝ ገዥ እንደራሴዎች ሲያደገድግ፣ ነፃነታችንን ያላስደፈርን ብቸኛ ሕዝብ ሆነን የተ ረፍነው ውርደትን አምርሮ የሚጠላ የመንፈስ ብርታት ስላለን ነው::ኢትዮጵያዊነት ከእዚህ ሌላ ምን ትርጉም አለው? ተዋርደን አንገዛም ነው የምንለው::

ለምነናል፤ ተማጽነናል፤ መለስ፣ ስብሃትና በረከት የራሳቸውን ህግና ህገ-መንግሥት እንዲያከብሩ:: ታሪካችንን ወደኋ ላ ቃኝተን፣ ትምህርት ወስደን፣ የእልህ፣ የቂም፣ የበቀል፣ የጥፋትና የውድመት አዙሪት ይብቃ ብለን ትህትናን ተ ላበስን «እባካችሁ ለሁላችንም የምትሆን ሰላም የነገሠባት፣ መብት የተከበረባት፣ ድህነት የተወገደባት ኩሩ ሀገር በጋራ እንገንባ» ብለን ተለማመጥን:: እንደ 1984ቱ የክልል ምርጫ የ97ቱም ሃገራዊ ምርጫ እንደሚጠምባቸው አውቀን፣ እንደልማዳቸው ደንብረው ሕዝብ እንዳይፈጁ፣ ከንብረታቸውና ከቀረ ሞገሳቸው ጋር በክብር ከስልጣን የሚወርዱበትን የማሪያም መንገድ ከፈትንላቸው:: በደም ሥራችን የሚፈሰው ደም በጀግንነት ውርስ የከበ ረ መሆኑን ዘንግተው፣ ለትህትናችንና ለአርቆ አሳቢነታችን፣ ለእርቅና ለድርድር ፍላጎታችን መለስና ጓደኞቹ የፍራቻ ልባስ አጠለቁለት:: ይህ የእብሪት እይታቸው በምርጫ 97 ሕዝብ በስልጡን መንገድ ያከናነባቸውን ሽንፈት በአግአዚ ጥይት እንዲቋቋሙት፣ ለመለስና ለሰቆቃ አምራች ኩባንያው ድፍረቱን ሰጣቸው:: ከ97 ምርጫ በኋላ በሕዝብና በሀገር ላይ የተፈጸመው ግፍ ጽዋውን ሞልቶ ፈሰሰ:: መለስ፣ ስብሃትና በረከት ሕዝብን አፍኖ በስልጣን ለመቆየት፣ በራሱ በዲያብሎስ ለመጋለብ ዝግጁ መሆናቸውን አሳዩ:: ይህንን የተረዳን ዜጎች ቁጭ ብለን መከርን:: አቅማችንን አሰባሰብን፣ እኛ ለምነን ሳይሆን እነመለስ የጨው ምሳሌ ገብቷቸው ወደ ድርድሩ ጠረጴዛ እንዲመጡ፣ እምቢም ካሉ እንዲወገዱ ማድረግ አለብን አልን:: አሁንም መለስና በረከት እንደልማዳቸው ፈንጂ ወረዳ ገብታችኋ ል፣ እንመትራችሁ ቢሉ ግን ውርድ ከራስ እንላለን:: ራስን መከላከል ደግሞ ከእንስሳት ጋር የምንጋራው መብት ሳይሆን አባዜ እንጂ::

ግንቦት 7 ስንሰኝ፣ ለአሥርተ-ሰዓታት ላንቃቸው በውሃ ጥም ደርቆ፣ በብብታቸው የምርጫ ካርዳቸውን ደብቀው፣ የአዲስ ቀን ተስፋ ሰንቀው፣ ለለውጥ እግራቸው እስከሚዝል የተሰለፉትን አረጋውያንና ባልቴቶች፣ ሲቪሎችና ወታደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶችን፣ የተስፋ ስንቃችሁ ተቀምቶ አይቀርም ለማለት ነው:: አዎን ባለፉት ሦስት ዓመታት፣ ብዙዎች የተስፋቸውን ውጤት ሳያዩ ከሕይወት ተለይተውናል:: ያለፉቱ፣ ለሰዓታት በመቆም ታሪክ በሠሩበት ቀን፣ በግንቦት 7 ስም በመሠረትነው ሕዝባዊ ንቅናቄ፣ የዕብሪተኞችን ተራራ ልንደረምስ መነሳታችንን ልናበስራቸው ቆርጠናል:: ግንቦት ሰባት የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ እምቢ ለእብሪት፣ እሺ ለሁሉም ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት፣ እሺ ለሁለገብ የትግል ስልት፣ እሺ ከብልጣብልጥነት ነጻ ለሆነ፣ የዜጎችን መብት ከምር ለተቀበለ፣ ሀገራዊ ድርድርና ስምምነት ይላል :: ዓላማው ቀና፣ ጥሪው ሀገራዊ ነው

# ግንቦት 7፤ የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

## ድርጅታዊ የፖለቲካ መርሐ-ግብር

### 1- መግቢያ

ለምዕተ ዓመታት በዘለቀው የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሥርአት ውስጥ የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ከተገዥነት አልፎ በዜግነት ደረጃ የታየበት አንድም ጊዜ የለም። በተመሳሳይም በየጊዜው ሥልጣን በጉልበታቸው ለመያዝ የቻሉና መንግሥታዊ ስርአቱን የተቆጣጠሩ ኃይሎች ራሳቸውን ገዥዎች አድርገው ከማቆየት ያለፈ ፍላጎት አሳይተው አያውቁም። በገዥዎች ዓይን፣ በተገዥነት የሚታይ ሕዝብ ከዜግነቱ የሚመነጩ መብቶች የሉትም። ገዥዎቹም በጉልበት በሚይዙት ሥልጣን፣ በሀገራችን የማህበራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚፈጽሟቸው ተግባራት በሙሉ ከራሳቸው ፍላጎትና ጥቅም ጋር የተሳሰሩ ብቻ ናቸው። እነዚህ ገዥዎች እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ መብት እንዳለው ዜጋ እንዲያዩ፣ ተግባራቸውንም የዜጋውን ፍላጎትና ጥቅም ለመጠበቅ የሚያስገድዳቸው የሞራል፣ የአመለካከትና የመዋቅር ልጓም ኖሮ አያውቅም።

ሕዝብም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ራሱን በገዥዎቹ መልካም ፈቃድ ብቻ የሚኖር አድርጎ እንዲቀበል የተጫነበትን የአመለካከት ሸክም ተቀብሎ ሲኖር ዘመናት ተቆጥረዋል። ገዥዎቹ የሚፈጽሙትን በጎም ሆነ ክፉ ነገር በአብዛኛው ተቀብሎ መኖርን እንጂ ሌላ አማራጭ መኖሩን ማሰብ በማይችልበት ረጅምና አስከፊ የጭለማ ዘመን ውስጥ ኖሯል።

የአገዛዝ መንግሥት ሥርአት በሰፈነበት ሀገር፣ ሕዝብ ከድህነትና ከድንቁርና ልገላገል፣ ሰብአዊና የሲቪል መብቶቼና ነፃነቶቼ ይከበሩልኝ የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ ሥርአቱ አይፈቅድም። ሕዝብ በራሱ ስሜትና ፍላጎት ተነሳስቶ የመብት ጥያቄዎች ካነሳ የአገዛዙ ምላሽ ሰልጣን ላይ ያወጣውንና ስልጣን ላይ መቀጠል ያስቻለውን ከፍተኛ የጉልበት ኃይል በመጠቀም ማፈን ብቻ ነው። በሀገራችን ዛሬም በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት ያለፉት የአገዛዝ መንግሥታዊ ሥርአቶች ዝርያ በመሆኑ የዜጎች መብትን በተመለከተ ያለው አቋም ካለፉት የአገዛዝ ሥርአቶች የተለየ አይደለም። ሕዝብ ገዥዎች በቸርነታቸው ከሚወረውሩለት የመብትና የደህንነት ፍርፋሪ ውጭ ፣ በዜግነቱ ሊጠይቃቸው የሚገቡ መብቶች አሉት የሚል እምነት ዛሬም በሥልጣን ላይ ያሉት የሀገሪቱ ገዥዎች ዘንድ አይታወቅም። በመሆኑም ሕዝብ የገዛ ሀገሩና የገዛ ሕይወቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለመምከርና ለመወሰን መብት የለህም ተብሎ በባይተዋርነት እንዲኖር ተገዷል። ይህ ደግሞ ጉልበቱን፣ ዕውቀቱንና ሃብቱን በነፃነት መንፈስ በማንቀሳቀስ፣ ከዓመት ወደ ዓመት እየተባባሱ የሚሄዱትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቹን ማቃለል እንዳይቻል ትልቁ እንቅፋት ሆኖበታል።

ይሁንና፣ በየደረጃውና ለረጅም ግዜ በተለያዩ ዘርፎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረገው ትግል፣ የተገዥነት ስብእናውን አውልቆ በዜግነቱ የሚገባውን ያልተሸራረፈ መብት ከሚጠይቅበት ደረጃ አድርሶታል። በእዚህ አቅጫጫ በቅርቡ በምርጫ 97ና ከእዛ ም በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የተከሰቱት ኩነቶች በሙሉ ሕዝብ በታሪኩ ያደረጋቸው ትግሎች ድምር ውጤት ከፍተኛ መገለጫዎች ናቸው።

ዛሬ በሀገራችን ያለውን የተወሳሰበ ሁለገብ ችግር አሳሳቢ ደረጃ ላይ ያደረሰው ሕዝብ በመንግሥት ሥርአቱ አመሠራረትና በሥርአቱ እንቅስቃሴ ላይ ወሳኝነት ያለው ሚና መጫወት አለመቻሉ ነው። ከችግሮቻችን ሁሉ መሠረታዊ የሆነው ችግር ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር የተሳሰረው ችግር ሆኗል። ዛሬ በሀገራችን በአንድ በኩል ራሱን ከተገዥነት አላቆ ሙሉ የዜግነት መብቱ እንዲከበርለት የሚፈልግ ሕዝብና በሌላ በኩል የገዥነት አባዜውን አራግፎ ሕዝብ በዜግነቱ የሚጠይቃቸውን መብቶች ለማክበር ፈቃደኛ ያልሆነ መንግሥታዊ የአገዛዝ ሥርአት ተፋጠው ቆመዋል። ይህ ችግር በጊዜ መፍትሄ ካላገኘ በሀገራችን ውስጥ የሚታየውን አጠቃለይ ቀውስ ከእዚህ በፊት አይተናቸው ከምናውቃቸው ቀውሶች በላይ የከረረና የናረ ደረጃ ላይ እንደሚያደርሰው ጥርጣሬ ሊኖረን አይገባም። ይህ ቀውስ አንዱን ወገን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ ሳይሆን ለሁሉም አጠቃላይ ወድመትን ሰንቆ የሚነሳ፣ ለማሰብ እንኳን የሚዘገንን መጥፎ መዘዝ ያረገዘ ነው።ይህ ቀውስ በሀገራችን ክልል ታጥሮ የሚቀር ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የሚገኘውን ሰላምና መረጋጋት ጎብኝቶት የማያውቀውን የአፍሪቃ ቀንድ ጭምር ወደባሰ ቀውስ እንደሚዶለው መተንበይ አያስቸግርም። ማዕከላዊ ከሆነው ፖለቲካዊ ችግር ባሻገር የሀገራችንን ሕዝብ ተብትበው የያዙት መልከ ብዙ ችግሮች በርካታ ናቸው። የኢኮኖሚ ድህነቱ አስከፊነት በየጊዜው በሚከሰተው ረሃብና ሰቆቃ ይገለጻል። በወባ፣ በሳንባ-ነቀርሳ፣ በኤድስና ከንጹህ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ጋር በተያያዙና በሌሎች ምክንያቶች በየቀኑ እንደቅጠል የሚረግፈው የሕዝብ ብዛት የጤንነት ችግራችን ምን ያህል አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰ የሚያሳይ ነው። ማንበብና መጻፍ የማይችለው የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ ትምህርት ቤት መግባት የቻለው ደረጃውን የጠበቀ ዕወቀት መቅሰም አለመቻሉ፣ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ አንስቶ አስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ተምሮ የሥራ ዕድል የሚያጣው ወጣት ከ80% በላይ መሆኑ፣ የገጠሩን ድህነት መሸከም ያልቻለው ሕዝብ ወደ ከተሞች በመፍለስ በሥራ አጥነት የሚርመሰመሰውን ባተሌ ቁጥር የሚያስፈራ ደረጃ መድረሱ፣ ማህበራዊ ችግሮቻችን አስፈሪ መሆናቸውን ይገልጻሉ። በሕዝብና በሀገር ሃብት ላይ ጥቂቶች ብቻ እንዳሻቸው የሚያዙበት፣ ያለማንም ተቆጣጣሪ እንዳሻቸው የሚዘርፉበት ሁኔታ፣ የሀገሪቱ ዜጎች በደልና ጥቃትን አቤት የሚሉበት የፍትህ ሥርአት አለመኖር፣ የኅብረተሰባችንን ቅስም እየሰበረና ተስፋ እያስቆረጠ የቆየ የሞራል አቋሙን እየናደ እንደ ሀገርና አንደ ሕዝብ ህልውናችንን እየቦረቦረ ይገኛል።

በሀገር ውስጥ የተፈጠረው በአድልኦና በዘረኛነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መዋቅር፣ በርካታ ዜጎችን በገዛ ሀገራቸው ባይተዋር እንዲሆኑ በማድረግ ምርጫቸው ዕውቀታቸውንና ጥሪታቸውን እየቋጠሩ በገፍ እንዲሰደዱ በማደረግ ላይ ነው። ሕዝብ ባለቤትነቱን በተቀማበት ሀገር፣ የተፈጥሮ መራቆትን የሚያስቆመው ጠፍቷል። የሀገርና የወገን ብሔራዊ ክብርና ጥቅም ጥቂት የስልጣን ሱሰኞችን ጥም ለማርካት ሲባል እየተረገጠና እየተቸረቸረ ነው።

ወደ ገጽ 4 ዞረሯል

*መርሑ- ግብር ከገጽ 3 የቀጠለ*

ህልቆ መሳፈርት የሌለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግራችን ዘሮ ዘሮ የሚመነጨው ቀደም ብለን ከጠቀስነው ሕዝብን በዜግነት የሚያስተናግድ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ዜጎች በሕይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በጥረታቸው ማቃለል የሚችሉበት የፖለቲካ ሥርአት ባለመኖሩ ነው።

ንቅናቄያችን ከሁሉም ችግሮቻችን ለይቶ በፖለቲካ ችግራችን ላይ ብቻ ያተኮረ መርሓ ግብር እንዲነድፍ የተገደደበት ሁኔታ የመነጨውም ከእዚሁ ፖለቲካውን የችግራችን መንስኤና መፍትሄ ቁልፍ አድርጎ ከማየት ከተደረሰበት ድምዳሜ ነው።

***ግንቦት 7፤ የፍትህ የነፃነትና የዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ*** ሙሉ ትኩረቱን የፖለቲካ ችግራችንን በመፍታቱ ጉዳይ ላይ ያደርጋል ስንልም ፣ ከፖለቲካው ጉዳዮች መሀል ለይቶ የሚያያቸው መሠረታዊ የፖለቲካ ነጥቦችንም አስቀምጦ ነው። እነዚህ መሠረታዊ ነጥቦች የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ለዘመናት ያደረጋቸውን ያልተሳኩ ትግሎች በመገምገም የተደረሰባቸው ናቸው። በተለይ ደግሞ በ1997 ብሔራዊ ምርጫ ሕዝብ እራሱን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ያደረገው ትግል የደረሰበትን ከፍተኛ የዕድገት ደረጃና ይህ ትግል የጋጠሙትን እንቅፋቶች የተለየ ትኩረት ሰጥቶ በመመርመር የተደረሰባቸው ነጥቦች ናቸው።

በምርጫ 97 የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ለመዘርጋት ችሎታ፣ ብቃቱና ጽናቱ እንዳላው አረጋግጧል። ሕዝብ የስልጣን ባለቤት መሆን ያልቻለው የሰጠውን ድምፅ በገለልተኛነት የሚቆጥርለት በማጣቱ ነው። በደምፅ ቆጠራ ሂደት ችግር ሲፈጠር አቤት የሚልበት ገለልተኛ ፍርድ ቤት ባለማግኘቱ ነው። ሕገመንግሥታዊ መብቱን ተጠቅሞ የደረሰበትን የምርጫ ድምፅ ዘረፋ በተቃወሞ ስብሰባዎችና ሰልፎች፣ በሥራ ማቆም አድማዎች መግለጽ እንዳይችል በገዥው ፓርቲ ፍላጎት በሚዘወሩ የጎሊስና ሕግመንግሥታዊ ነፃነት በሌላቸው የመከላከያ፣ የስለላና የፖሊስ ኃይሎች በመታፈኑ ነው። ምሬቱን ቁጭቱንና በደሉን የሚያሰማበት ነፃ የሆነ የመገናኛ ብዙሐን በሀገሩ እንዳይኖር በገዥው ፓርቲ በመደረጉ ነው። እነዚህ ቁምነገሮች የንቅናቄያችንን ዓላማና ግብ፣ ወደ እንቅስቃሴው ግብ ለመጓዝ የምንከተላቸውን የትግል ስልቶችና መርሆች፣ ድርጅታዊ አወቃቀሩንና አሠራሩን ወስነውታል

## 2- **የፖለቲካ ግብ፤**

ዓላማችን የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ሳይሆን በሀገራችን ፖለቲካ ያገባኛል ከሚሉ ሁሉም ኃይሎች ጋር በመተባበር የመንግሥት ስልጣን የሚያዝበትን አግባብ በሕዝብ ነፃ ፍላጎትና ውሳኔ የሚገዛ፣ ሰላማዊ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ሥልጣን አያያዝ ሂደት በሀገራችን ለማስጀመር ነው።

ዓላማችን በሀገራችን እንዲጀመር የምንፈልገው ሰላማዊ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥልጣን አያያዝ ሂደት ብልጭ ብሎ እንደገና በአምባገነንነት ግርሻ መልሶ የሚጠፋ እንዳይሆን የሚጠብቁ ነፃ መንግሥታዊ ተቋማት፣ ነፃ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል፣ ነፃ ፍርድ ቤት፣ ነፃ የምርጫ ቦርድ፣ በፖለቲካ ኃይላቱ ስምምነትና በሕዝብ ንቁ ተሳትፎ የሚመሠረቱበትን ሁኔታ በቅድሚያ ለመፍጠር ነው።

ዓላማችን ነፃ የሆኑት መንግሥታዊ ተቋማት እንዲቋቋሙ፣ የሚቋቋሙትም ነፃነታቸው ተከብሮ እንዲቀጥል፣ ራሳቸውም ነፃ ተቋማት ሆኑ እንዲሁም በሕዝብ ፍላጎትና ምርጫ የሚፈጠረው አስተዳደር፣ በህግና በውክልና ከተሰጠው የስልጣን ገደብ በማለፍ ችግር እንዳይፈጥር ቁልፍ መከላከያ የሆነውን የመገናኛ ብዙሐን ነፃነት ለማስከበር ነው።

ዓላማችን ሕዝብ ነፃነቱን ለመከላከል አቅም የሚሰጡትን የራሱን ነፃ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ተቋማትን የሚፈጥርበትንና የሚያጠናክርበትን፣ በጥቅሉ የሲቪል ማህበረሰብ ግንባታ ሂደት የሚፋጠንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ነው።

## 3- **ንቅናቄያችን፣ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚገለገልባቸው መሠረታዊ እሴቶች፤**

ፍላጎታችን የሁሉም ዜጎች የግለሰብ መብት በእኩልነት የሚከበርበት፣ ሁሉም ዜጎች በህግ ፊት በእኩልነት የሚታዩበት፣ ሁሉም ዜጎች እኩል የሆነ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ መብቶች ያላቸው መሆኑን የመቀበል እምነት የአዲሱ መንግሥታዊና ፖለቲካዊ ሥርአት የማዕዘን ድንጋይ እንዲሆን ነው።

ፍላጎታችን መሠረታዊ የሆኑት የግለሰብ መብቶች በሚከበሩበት የፖለቲካ ማእቀፍ ውስጥ ባህልን የማበልጸግ፣ ቋንቋን የማሳደግ፣ የመጠቀምና እንዲሁም ራስን በራስ የማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካና የባህል መብቶች በተግባር እንዲተረጎሙ ለማድረግ ነው።

ፍላጎታችን በሀገራችን የሚገኙ የበርካታ ዘውጌ ማህበረሳባት ቋንቋዎች፣ ባህሎችና እምነቶች የውበታችን መገለጫ እንጂ የልዩነታችን መሠረቶች ሆነው ለሁላችንም ድክመትና ውድመት መሣሪያ እንዳይሆኑ ለማደረግ ነው። የዘውግ እኩልነት የመብት ጥያቄዎች በሀገራችን ሉዐላዊ አንድነት ክልል ውስጥ፣ በሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች የተባበረ ትግል መፍትሄ የሚያገኙበት ብቸኛው አማራጭ ሆኖ በሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ተቃባይነት እንዲኖረው ለማድርግ ነው።

ፍላጎታችን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፋፍሎ ለመግዛት ሲባል የዘውግ ልዩነቶቻችንን ምክንያት በማድረግ በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ የሚያሰራጨውን መርዘኛና አደገኛ የዘረኛነት አመለካከት ሕዝብናየተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲገነዘቡት በማድረግ የዘረኛነት መርዝ ከሕበረተሰባችን ውስጥ በጊዜ ለመንቀል ነው።

ፍላጎታችን ሕዝብ በዜግነቱ የሚጠይቃቸው መብቶች፣ በነፃ ሃሳብን የመግለጽ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ያለፍራቻ የመሥራት፣ የመኖር፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብቶች እንዲከበሩ፣ የህግ የበላይነት የሰፈነበት፣ ሕዝብ በሀገር ይሁን በመንደር ደረጃ

ወደ ገጽ 5 ረሯል

*መርሐ- ግብር ከገጽ 4 የዞረ*

የሚያስተዳድሩትን የመምረጥ መብት የሚጎናጸፍበት፣ ሕዝብ የፈለገውን የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመፍጠርና የመከተል ነፃነቱ እንዲጠበቅ፤ እነዚህ የመብት ጥያቄዎች ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጎች፣ ያለምንም የዘውግ፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የፆታ፣ የዕድሜና የፖለቲካ አመለካከት ልዩነቶች በተግባር እንዲተረጎሙ ለማድረግ ነው። በጥቅሉ የሀገራችን ሕዝብ እንደ ዜጋ ታይቶ መብቶቹ እንዲከበሩለትና የገዛ ሕይወቱን በሚመለከቱ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን እንዲቀዳጅ ለማድረግ ነው።

4- **<u>የንቅናቄያችን የትግል ስልትና መርሆች</u>**

ትግላችን ቀኖናዊ በሆነ መንገድ የሚከተለው የትግል ስልት የለውም። የሀገራችንን ተጨባጭና የተለየ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ማንኛውንም ዓይነት ሁለገብ የሆነ የትግል ስልት በተግባር ያውላል። የትግል ስልት ምርጫችን የግፍ አመጻቸውን በሕዝብ ላይ የሚያዘንቡ ገዥዎችና ደጋፊዎቻቸው በሚያኪያሂዱት የህግና ሴላም ማስፈራሪያ የማይታቀብ ይሆናል። በሌላ ጎኑ ንቅናቄያችን የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ 97 በገዥዎቹ ላይ የተጎናጸፈውን የሞራል የበላይነት እንዲከበር ያደርጋል። በቅርብ ጊዜ በሀገራችን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሞክሮ የነበረውን ሰላማዊ የትግል ስልት ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመገምገም መስተካከል ያለበትን በማስተካካል ይህን የትግል ስልት እንደአስፈላጊነቱ በሥራ ላይ ያውላል። ሰላማዊ ትግል ሲባል ግን በስልጣን ላይ ያሉት ገዥዎች ሰላማዊ ነው ብለው እንዳሻቸው በሚደነግጉልን አፋኝ ህግ የሚገዛ እንደማይሆን፣ ህገወጥ የሆኑ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በቂ ዝግጅት በተደረገበት የሕዝባዊ ሰላማዊ እምቢተኛነት እርምጃዎች በመጣስ የሚከናወን መሆኑን ያረጋግጣል።

ትግላችን፣ በሀገራችን የነገሡት አምባገነን ገዥዎች የፍትህ ሥርአቱን፣ የመከላከያ፣ የደህንነቱንና የፖሊስ ኃይሉን እንዳሻቸው በሚጠቀሙበት ሁኔታ የሚደረግ ነው። ትግላችን ዜጎች መብታቸውን፣ ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን ህገወጥ ከሆነ የገዥዎች ጥቃት የሚከላከሉበት ሥርአትና ተቋማት እንዳይኖሩ በተደረገበት ሁኔታ ውስጥ የሚካሄድ ነው። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ የሚደረግ ትግል ሕዝብን ቀጥ ከሌለው የአምባገነኖች ጥቃት ለመከላከል የሚቻልበት ስልትና ዝግጅት ያስፈልገዋል። ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ንቅናቄያችን እራሱን ከእንዲህ ዓይነቱ ጥቃት መከላከል የሚችልባቸውን ዘዴዎች ያጤናል፣ በሥራ ላይም ያውላል።

5- **<u>ንቅናቄያችን ከሌሎች መሰል የፖለቲካ ኃይላት ጋር ለሚያደርገው ትብብር የሚገለገልባቸው መሠረታዊ እሴቶች</u>**

- ***የግንቦት 7*** ንቅናቄ በቅድሚያ ማናቸውም በሀገሪቱ ፖለቲካ ያገባኛል የሚሉ ኃይሎች፣ በስልጣን ላይ ያለው መንግሥታዊ አገዛዝ ጭምር የሀገራችን ሕዝብ በዜግነት እንጂ በተገዥነት መኖርን የማይቀበል መሆኑን ተረድተው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዜግነቱ የሚገቡት መብቶች ተከብረውለት ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚፈጠረው የሕዝብ ምስፍንና ላረጋገጠ መንግሥታዊ ሥርአት ሁላችንም በጋራ እንድንሠራ ነው።
- ንቅናቄያችን በሀገራችን ፖለቲካ ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድነት ተባብረው መሥራት ይገባቸዋል ብሎ ያምናል። እነዚህ ኃይሎች በመወያየትና በመግባባት መፈጠር ለሚገባው ሰላማዊ፣ ህጋዊና የሰለጠነ የሽግግር መድረክ በጋራ መታገል ይኖርባቸዋል።
- የፖለቲካ ኃይሎቹ ትብብር ዋና ዓላማ ስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ አስገድዶ ወደ ድርድር ለማምጣት ይህ ካልሆነም፣ አገዛዙን በሁለገብ ትግል በማስወገድ በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ ሂደትን ለማስጀመር ቁልፍ መሣሪያ ነው። የሚፈጠረው ትብብር መድረኸ በሥልጣን ላይ ያለውን አምባገነናዊ አገዛዝ ማውረድ ብቻ ሳይሆን፣ በቦታው ዴሞክራሲያዊ መንግሥታዊ አስተዳደር በኢትዮጵያ ለመተካት እስከሆነ ድረስ፣ የትብብሩ አባላት በሙሉ በጋራ የሚስማሙባቸው የማይጣሱና የማይገሰሱ የትብብሩ የፖለቲካ እሴቶች በቅድሚያ መቀመጥ አለባቸው። እነዚህ እሴቶች፣ የኢትዮጵያን ሉዐላዊ አንድነት መቀበል፣ የፖለቲካ ሥልጣን፣ በሀገር አቀፍ ይሁን ከዚያ በታች በሚገኙ አስተዳደራዊ አሃዶች ውስጥ የሚያዘው ዜጎች በእኩልነት በሚሰጡት የአንድ ሰው አንድ ድምፅ ሥርአት መሆኑን ማመን፣ የትብብሩ የትግል ዓላማ ሥልጣን ለመያዝ ሳይሆን ሥልጣን በሕዝብ ፈቃድ የሚያዝበትን ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለማመቻቸት መሆኑን መቀበል ናቸው። ንቅናቄያችን እነዚህን መሠረታዊ እሴቶች ከተቀበሉ ማናቸውም ዓይነት ተመሳሳይ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲዎች ከሷቸው፣ የራሳቸው የሆኑ አደረጃጀቶችን የሚጠቀሙና የትግል ስልት የሚከተሉ የፖለቲካና ፖለቲካዊ ካልሆኑ ቡድኖች ጋር በትብብር ለመሥራት ፈቃደኛ ነው። ለዚህም ዕውን መሆን ጥረት ያደርጋል።
- ንቅናቄያችን የሀገራችንን ሕዝብ ከመንግሥታዊ የአገዛዝ ሥርአት ወጥቶ በሕዝብ ምስፍንና ላይ ወደ ተመሠረተ መንግሥታዊ የአስተዳደራዊ ሥርአት ለመሸጋገር ያለውን ፍላጎት በዋነኛነት የዘጋው በሥልጣን ላይ ያለው ገዢ ፓርቲ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ይህንን ተረድተው ከዚህ ገዢ መንግሥት ጋር የሚደረግ የተቃዋሚዎች ትግል በቅድሚያ ማተኮር የሚገባው ሕዝብ ወሳኝ መሆን የሚችልበትን አጠቃላይ የነፃነት ሁኔታ መፍጠር፣ እንዲሁም ይህንን ነፃነት የሚንከባከቡ ተቋማት ማቆም መሆኑን ከተቀበሉና ይህንን ቁልፍ የፖለቲካ ቁምነገር መርሐቸው አድርገው በአደባባይ ከሚወጡ፣ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ለመሥራት ዝግጁ ነው። የፖለቲካ ድርጅቶቹ በዚህ መንገድ ለመሄድ ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ ንቅናቂያችን ሁሉንም ድርጅቶች በእኩልነት ለማስተናገድ ፈቃደኛ ነው።
- ንቅናቄያችን ከላይ የተቀመጠውን ወሳኝ የፖለቲካ አጀንዳዎች የጋራ አጀንዳቸው አድርገው ለመንቀሳቀስ ፍላጎት ካላቸው በውጭ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የድጋፍ ድርጅቶችና የሰብአዊና የሲበቪል መብቶች ተከራካሪ ቡድኖችና ሌሎች የሲቪል ማሕበራት ጋር በጋራ ለመሥራት ይጥራል።
- ንቅናቂያችን ዓላማውን በውጭ ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ በማስተዋወቅ፣ ሰፊ ዓለም አቀፍ የድጋፍ ድርጅቶች መዋቅር በዓለም ላይ ይዘረጋል። እነዚህ የድጋፍ ድርጅቶች ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ደጋፊዎች ጋር በንቅናቂያችን ዋንኛ አጀንዳ ዙሪያ በጋራ እንዲሠሩ ትልቅ ጥረት ያደርጋል።

6- **<u>የንቅናቂያችን የእርቅና የመቻቻል እሴቶች፣</u>**

ትግላችን በሁኔታዎች አስገዳጅነት በሀገራችን ውስጥ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ ባለመቻላቸው የተነሳ ሌሎች ሁለገብነት ያላቸውን የትግል ስልቶችን የመረጡና ወደፊትም በተመሳሳይ ምክንያት ሊመርጡ የሚችሉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች በሰላማዊ የትግል ስልት ውስጥ የተካተቱን የመቻቻልን፣ የመደራደርን፣ ልዩነትን የማጥበብን፣ ለሰለማዊ መፍትሄዎች ቅድሚያ መስጠትን፣ ባለጋራንና ደጋፊዎቹን አለማስበረገግን የመሳሰሉትን መሠረታዊ እሴቶች የእንቅስቃሲያቸው መመሪያዎች እንዲያደርጓቸው ግፊት የሚያደርግ ይሆናል። በተለይ በሥልጣን ላይ ያሉት ገዥዎች የፈጠሩት መርዘኛ የዘር ፖለቲካ በባህላችን ከኖረው በደልን በአመጽ ከመመከት ባህላችን ጋር ተደምሮ ሕብረተሰባችንን መውጫ ከማይኖረው የእልቂትና ውድመት ገሃነም ውስጥ እንዳያስገባው ንቅናቂያችን ሁሌም ልዩነቶችን በውይይት፣ በድርድርና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት በየወቅቱ ለመፈጠሩ እውነተኛ እድሎች በሩን የማይዘጋ ይሆናል።

7- **<u>ንቅናቂያችን የሚታገላቸው ጎጂ ባህሎች</u>**

በሀገራችንና በታሪካችን ተከስቶ የማያውቅ በሕዝብ ምስፍንና ላይ የቆመ መንግሥታዊ የአስተዳደር ሥርአት የመመሠረት ዓላማ ማሳካት የሚቻለው፣

መርሓ ግብር ከገጽ 5 የዞረ

በቀድሚያ ተከታታይ የአገዛዝ ሥርአቶች የሥልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ በህብረተሰባችን ውስጥ ተንሰራፍቶ እንዲቀጥል ካደረጉት የጥርጣሬ፣ ራስን ብቻ የማስቀደም፣ እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ፣ የመሰሪነትና ሌሎችንም ጎታችና ጎጂ ባህሎች ሁላችንም አውልቀን ስንጥል ብቻ እንደሆነ ንቅናቂያችን ያምናል። አንዱ ወገን የሌላውን ወገን ጭንቀቶች፣ ፍራቻዎች፣ ፍላጎቶች በቀና መንፈስ አዳምጦ፣ በመቀራረብና በመግባባት ለመፍትሄዎቻቸው በጋራ መሥራት አማራጭ የሌለው የአንድነት ጎዳና መሆኑን ይቀበላል።

ንቅናቂያችን የሀገራችንን ሕዝብ የገጠሙት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፈተናዎች ግለሰቦች ይሁኑ ጥቂት ቡድኖች በተናጥል፣ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ብቻ የሚታለፉ እንዳልሆኑ ይረዳል። ብንወድቅም ብንነሳም በአንድነት ብቻ እንደሆነ ይገነዘባል። መተባበር፣ ጊዜያዊ ጥቅም ማስገኛ ሳይሆን፣ ዘለቄታዊነት ላለው የተረጋጋ እና የበለጸገ ፍትሃዊ የሆነ ሀገርና ማህበረሰብ ለመፍጠር ወሳኝ መሆኑን ንቅናቂያችን ከልብ ይቀበላል።

## ጥሪ ለኢትዮጵያ ሕዝብ።

ነፃነትና ፍትህ፣ ትምህርትና የጤና አገልግሎት፣ ሥርቶና ጥሮ ግሮ ኑሮን ማሻሻልና መበልጸግ፣ እነዚህና ሌሎችም መብቶች በዜግነትህ ልታገኛቸው የሚገባ እንጂ እንደመርገም በራስህ ላይ የሚከመሩ ገዥዎች የሚቸሩህ አይደለም። ማንም ገዥ እነዚህን መብቶችህን እንዳሻው ሊሰጥ እንዳሻው ሊከለክል ልትፈቅድለት አይገባም።

ገበሬው የመንግሥት ጭሰኛ ሳይሆን የመሬት ባለቤትነት መብቱ የተከበረ፣ የማዳበሪያና የእርሻ መሣሪያ፣ ሌሎችንም ቁሳቁሶች አግኝቶ በነፃነት ሠርቶ የሚኖርብት፤

ላብአደሩ ለድካሙ ተመጣጣኝ ክፍያ የሚያገኝበት፣ የሥራ ቦታ ደህንነቱ የተጠበቀበት፣ ጥቅሙንና ፍላጎቱን የሚንከባከብበት፣ በነፃነት ያቆመው የራሱ የሙያ ማህበር ባለቤት በመሆን በትጋት የሚያመርትበት፤

ተማሪውና አስተማሪው የዜግነት መብታቸው በተከበረበት የአካደሚክ ነፃነት በሰፈነበት የመማርና የማስተማር ሂደቱም ደረጃው በተጠበቀበት ሁኔታ ዕውቀት የሚገበያዩበት፤

ነጋዴውና ባለፋብሪካው ያለምንም አድልኦ ለሁሉም ባለሃብት በእኩልነት በተደላደለ የመፎካከሪያ ነፃ ገበያ በሥራቸው እየተወዳደሩ የሚበለጽጉበት፤

ዳኞች ለሙያቸው ክብር ያላቸው፣ የፖለቲካ ሹመኞችን ፊት እያዩ ሳይሆን፣ በነፃነትና በልበሙሉነት ለተጻፈው ህግና ለፍትህ እንዲሁም ለኅሊናቸው ብለው ብይን የሚሰጡበት፤

በመንግሥታዊ የሲቪልና የወታደር ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የመንግሥት ሠራተኞችና የመከላከያ ኃይል አባላት የሥራ ዋስትናና የእድገት ደረጃ መሻሻል ከዘረኛነትና ከአድልኦ በጸዳ፣ በችሎታና በጥረት መመዘኛ ዋንኛው መለኪያ በሆነበት ሁኔታ ሕዝብን የሚያገለግሉበት፤ በአጠቃላይ ሁሉም ዜጎች በፍላጎታቸውና በምርጫቸው የመሥራትና የመኖር ሰብዓዊ ነፃነታቸው የወያኔ/ ኢሕአዴግም ሆነ ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አሽከር፣ አደግዳጊና ፍለጎት ፈጻሚ በመሆን የሚያገኙት እርጥባን ሳይሆን፣ በዜግነታቸውና በሰውነታቸው የታደሉት መብት
መሆኑን የተቀበለ አዲስ የፖለቲካ ሥርአት ለመመሥረት ሁላችንም በጋራ እንነሳ።

በተለይ የመከላከያ ሠራዊቱ የሀገራችን አምባገነን ገዥዎች የስልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ ብቻ በሚጭሩት ጦርነት ውድ ሕይወቱን እንዳልባሌ ነገር በየቦታው የሚገብርበት አሰቃቂ ሁኔታ ማብቃት ይኖርበታል። ይህ ኃይል በራሱ የሚከፍለው መስዋዕትነት ሳያንሰው፣ በገዛ ወገኑ ላይ የግፍ እርምጃ እንዲወስድ እየተገደደ፣ የወገንና የሀገር መከታ ሳይሆን የአንድን ፓርቲ ጠባብ ጥቅሞች አስጠባቂ አስፈሪ ጭራቅ ሆኖ በሕዝብ የሚታይበት ሁኔታ እንዲያከትም ትግል ማድረግ ይኖርበታል። ዘለቄታዊ የሙያ፣ የቅጥርና የዕድገት ዋስትና እንደጠዋት ጤዛ ብን ብለው ከሚጠፉ አምባገኖነች ጋር በመለጠፍ የሚገኝ ሳይሆን ሕዝባዊ አጋርነትን በማረጋገጥ የሚሰጥ፣ ዘላለማዊ ክብር የተደረበበት ሽልማት መሆኑን መረዳት ይኖርበታል። የሕዝብ ነፃነትና መብት ሲጠበቅ የእርሱም ነፃነትና መብት እንደሚጠበቅ ተረድቶ ሕዝባዊ ትግሉን ለመደገፍ ቆርጦ እንዲነሳ ልዩ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

***የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!***

ሁሉኑም ዜጎቿን በእኩልነት የምታስተናግድ፣ አንድነትዋን የጠበቀች፣ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት በምታደርገው ትግል በግንባር ቀደምትነት እስከ መጨረሻው አብረንህ ለመታገልና ለድል ለመብቃት ቆርጠን ተነስተናል።

ንቅናቂያችን ከፊታችን የተጋረጠው ፈተና ከባድ መሆኑን ይቀበላል። ይህም ሆኖ በሰው ልጆች የጋራ ጥረት የማይቃለል ምንም ዓይነት የጋራ ችግር የለም በሚለው የአብርሆት ራዕይ መሠረት ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን፣ በጽናት በመታገል በጋራ ወደ ዓለምነው ግብ እንደምንደርስ ንቅናቂያችን በጽኑ ያምናል።

*ግንቦት 7 2000*

# ዴሞክራሲያዊ ሥርአት በሀገራችን መገንባቱ አይቀሬ ነው!!!